## እውነተኛ የጌታ ኢየሱስ ደቀ-መዝሙርነት

**ደቀ-መዝሙር** ማለት የአንድ መምህር/ቡድን የሕይወት መርህ/አኗኗርና አስተምህሮ የሚከተል ሰው ማለት ነው፡፡

በወንጌላት ውስጥ ከሕዝቡና ከአለቆች መካካል እንኳ ሳይቀር ብዙዎች በጌታ ኢየሱስ ያመኑ ቢሆኑም ፈሪሳዊያን ያደርጉባቸው ከነበረው ማስፈራሪያ የተነሳ በእርሱ ማመናቸውን የማይገልጡ ነበሩ፡፡ ዮሐ 12፡42፤
አንዳንዶቹ ደግሞ የጌታ ኢየሱስ ይመጣል ተብሎ ይጠበቅ የነበረው መሲሁ መሆኑን በውል ሳይረዱ ባደረጋቸው ተዓምራዊ ሥራዎች ተጠቃሚ ስለሆኑ ብቻ ለአጭር ጊዜ ተከትለውታል፡፡ ዮሐ 6፡25-36፤

በአዲስ ኪዳን ውስጥ የጌታ ኢየሱስን አዳኝነት አምነው እርሱን መከተል የጀመሩ ሁሉ የጌታ ደቀ-መዛሙርት የተባሉበት ሁኔታም አለ፡፡ ከእነዚህ ውስጥ ለጥቂት ቀናት/ሳምንታት ወይም ወራት ይከተሉት የነበሩ በእርሱ ምክንያት የበረታ ስደት ደርሶባቸው ሳይሆን ጌታ ኢየሱስ ራሱ የሚያስተምረውን የአንድ ጊዜ ትምህርት ፍቺ በውል ስላልተረዱ ብቻ እርሱን መከተል ያቋረጡ አሉ፡፡

ዮሐ 6፥60-66፣ "ከደቀ-መዛሙርቱ ብዙዎች ይህን ሲሰሙ፣ "ይህ የሚያስጨንቅ ቃል ነው፤ ማንስ ሊቀበለው ይችላል?" አሉ;"…"ከዚህም በኋላ ከደቀ መዛሙርቱ ብዙዎች ወደ ኋላ ተመለሱ፤ ከዚያም ወዲያ አልተከተሉትም፡፡"

የተወሰኑት ደቀ-መዛሙርት ደግሞ የሰራቸውን ታምራዊ ስራዎች አይተው በስሙ ያመኑ ቢሆንም ጌታ ኢየሱስ ግን አይታመንባቸውም ነበር፡፡ ዮሐ 2፡23-25፣
ከዚህም አልፎ የእርሱ ተከታዮች እየተባሉ ለዓመታት የቆዩ ቢሆንም የእርሱ ደቀ-መዛሙርት መሆናቸውን የሚያስታውቅ የባሕርይ ለውጥ ያልታየባቸው፣ በመጨረሻም ከተቃዋሚዎቹ ጎን በመሰለፍ ጌታን ለማስገደል ከገዳዮቹ ጋር የተባበሩ ለመኖራቸው የአስቆሮቱ ይሁዳን በምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል፡፡

በሌላ በኩል አዲስ ከዳን ውስጥ ለጌታ ኢየሱስ ወንጌል ታላቅ ዋጋ በመክፈል ያገለገሉና ስለ ጌታ ፍቅር ሲሉ እስከ ሕይወት መስዋዕትነት ድረስ የከፈሉ ጥቂቶች አይደሉም፡፡ ስለዚህ የጌታ ኢየሱስ ደቀ-መዛሙርት የተባሉት በሁለት ከፍሎ ማየት/ማወቅ ያስፈልጋል ማለት ነው፡፡ እነርሱም እውነተኛ ያልሆኑ ደቀ-መዛሙርትና እውነተኛ ደቀ-መዛሙርት ናቸው፡፡

### እውነተኛ የጌታ ኢየሱስ ደቀ-መዛሙርት መለያዎች/የሚታወቁበት መጽሐፍ ቅዱሳዊ መስፈርቶች

1. የእግዚአብሔር አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ ማንነት ተረድተው የሚያምኑ፤ የሚታመኑትና የሚመኩበት፣ የሚያመልኩትም ከእግዚአብሔር አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ በስተቀር ሌላ የሚያመልኩት ምንም ፍጥረታዊ ነገር የሌላቸው ናቸው፡፡

ማቴዎስ 28፡19-20፣ ስለዚህ ሂዱና ሕዝቦችን ሁሉ በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤ [20] ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ አስተምሯቸው፤ እኔም እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁል ጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ።"

ቆሮ 1፡27-31፣ (ኤር 9፡23-24), "እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ጠቢብ በጥበቡ አይመካ፥ ኃያልም በኃይሉ አይመካ፥ ባለ ጠጋም በብልጥግናው አይመካ፤ 24 የሚመካ ግን፣ እኔ እግዚአብሔር እንደሆንሁ በማወቁና፣ በምድር ላይ ምሕረትን፣ ፍትሕንና ጽድቅን የማደርግ መሆኔን በመረዳቱ፣ በዚህ ይመካ፤ እኔ በእነዚህ ነገሮች፣ እደሰታለሁና፤" ይላል እግዚአብሔር።"

2. **ፍቅር፡ -**

***ሀ. ከማንኛውም የቤተሰብ አባል፣ የቅርብ ዘመድና ጓደኛ ይልቅ ጌታ ኢየሱስን (እግዚአብሔርን) የሚወዱ።***

ማር 12፡30-31፣ አንተም ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ፣ በፍጹም ነፍስህ፣ በፍጹም ሐሳብህና በፍጹም ኀይልህ ውደድ።'

ማቴ 10፥37 "ከእኔ ይልቅ አባቱን ወይም እናቱን የሚወድ ለእኔ ሊሆን አይገባውም፤ ከእኔ ይልቅም ወንድ ልጁን ወይም ሴት ልጁን የሚወድ ለእኔ ሊሆን አይገባውም፤"
ሉቃ 14፡26፣ "ወደ እኔ የሚመጣ ሁሉ አባቱንና እናቱን ሚስቱንና ልጆቹን፣ ወንድሞቹንና እኅቶቹን፣ የራሱንም ሕይወት እንኳ ሳይቀር ባይጠላ፣ ደቀ መዝሙሬ ሊሆን አይችልም፤"

***ማብራሪያ፡-***

***በማቴ 10፡37 እና ሉቃ 14፡26 ላይ የተጠቀሰው አንድ ሰው የቤተ-ሰቦቹ አባላት ባይጠላ ደቀ-መዝሙሬ ሊሆን አይችልም የሚለው ቃል፣ ማንኛውም አማኝ ቤተሰቦቹን በምንም ምክንያት መጥላት እንዳለበት ለማሳየት ሳይሆን፣ የቤተሰቦቹ አባላት የሚፈጽሙትን የኃጢአት ድርጊቶችን በመጥላት በሚያደርጉት የወንጌል ተቃዋሚነት ስራ አለመተባበርን ያመለክታል። ደግሞም ከቤተሰብ አባላትና ከጌታ ኢየሱስ አንዱን የመምረጥ አስገዳጅ ሁኔታ በሚፈጠርበት ጊዜ፣ ጌታ ኢየሱስን መምረጥ እንዳለበት የሚያሳይ ነው። ጌታ ኢየሱስ ይህን ትምህርት ባስተማረበት ወቅት የነበሩት አድማጮች ውስጥ ገና በእርሱ ያላመኑ ሰዎችና ተቃዋሚዎችን ሊያካትት ይችላል። ስለዚህ ሁሉንም አድማጮች የሚመለከት አይደለም ማለት ነው። የሚመለከታቸው ሰዎች ምሳሌ ለመጥቀስ ያህል፡ -***

1. ***አንድ ሰው በጌታ በማመኑ ምክንያት ቤተሰቦቹ ተቆጥተው በጌታ ማመኑን እንዲተው ግድ ቢሉት ቤተሰቦቸቹን ከኢየሱስና ከእግዚአብሔር ቃል ዕውነት ይልቅ ፈርቶም ሆነ ወዶ ጌታን መከተል ቢተው የጌታ ደቀ-መዝሙር መሆን አይችልም ማለት ነው።***

2. ቤተሰቦቹ በጌታ ያመኑት ወገኖችን ለማጥቃት ወይም የወንጌልን ስራ የሚቃረን ስራ ለመስራት ቢነሱና እርሱም በዚህ ጉዳይ ቤተሰቦቹን በአንዳች በማገዝ የተባበረ ከሆነ፣ ንጉስ ዳዊትን በማገዝ ከአባቱ ሴራ በተቃራኒ ለእግዚአብሔር ከቆመው የንጉስ ሳዖል ልጅ ዮናታን ከፈጸመው ድርጊት የማይስማማ ስራ ሰርቷል ማለት ነው። እንዲህ ዓይነት ለምርጫ አስቸጋሪ የሆኑ ሁኔታዎች በሚገጥሙ ጊዜ ኢየሱስን መምረጥ ለእውነተኛ ደቀ-መዝሙርነት ግዴታ መሆኑን የሚያሳይ ነው።
3. አንድ ቤተሰብ ያለው ደቀ-መዝሙር ጌታ ኢየሱስ ሙሉ ጊዜውን ሰጥቶ ቤተሰቦቹም ከሚኖሩበት አካባቢ ርቆ ወንጌልን እንዲያገለግል ቢመርጠውና ቢጠራው ከቤተሰቡ ጋር መቆየትና እነርሱን መርዳት በማስቀደም ጌታን አልታዘዝም ካለ እውነተኛ የጌታ ደቀ-መዝሙር አይደለም ማለትን የሚያመለክት ነው እንጂ፣ ጠላቶቻችሁን ውደዱ ያለ ጌታ ቤተሰብን እንዲጠሉ አይፈልግም።
   ጌታ ኢየሱስ ኃጢአትን የሚጠላ ሆኖ ሳለ ኃጢአተኞችን ከመውደዱ የተነሳ ሕይወቱን በመሰዋት ሊያድናቸው ነው ወደ ዓለም የመጣው። ዕብ 1፡9፣ ሮሜ 5፡8፤

**ለ. ባልንጀራውን (በጌታ ያመኑትና ያላመኑትን ማናቸውም ሰዎችን ሁሉ) እንደራሱ የሚወድ።**

ማር 12፡ 31፣ ሁለተኛውም ይህ ነው፤ 'ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ።' ከእነዚህም የሚበልጥ ትእዛዝ የለም።"

ዮሐ 13፡35 እርስ በርሳችሁ ብትዋደዱ ሰዎች ሁሉ የእኔ ደቀ-መዛሙርት እንደሆናችሁ በዚህ ያውቃሉ። (ማቴ 7፡15-19 በፍሬአቸው ታውቋቸዋላችሁ)

ሉቃስ 6፡27-28፣ "ነገር ግን ለእናንተ ለምትሰሙ እላችኋለሁ፤ ጠላቶቻችሁን ውደዱ፤ ለሚጠሏችሁም መልካም አድርጉ፤ [28] የሚረግሟችሁን መርቁ፤ ለሚበድሏችሁም ጸልዩ።

**ሐ. ከራሱ ሕይወት ይልቅ ጌታ ኢየሱስን የሚወድ፤**

ሉቃስ 14:26-27 ማንም ወደ እኔ የሚመጣ ቢኖር አባቱንና እናቱን ሚስቱንም ልጆቹንም ወንድሞቹንም እኅቶቹንም የራሱን ሕይወት ስንኳ ሳይቀር ባይጠላ፥ ደቀ መዝሙሬ ሊሆን አይችልም።"

**መ. ከማንኛውም ሀብትና ንብረቱ፣ የስልጣን ስፍራና፣ ድሎቱ ይልቅ ጌታ ኢየሱስን የሚወድ።**

ሉቃስ 14፥33 "እንግዲህ እንደዚሁ ማንም ከእናንተ ያለውን ሁሉ የማይተው ደቀ መዝሙሬ ሊሆን አይችልም።" (ይህም በተለይም ለሙሉ ጊዜ አገልግሎት የተጠሩትን የሚተዳደሩበትን ሥራ፣ ያላቸውን ሃብትና ንብረት ሁሉ ትተው የእርሱን ጥሪ ማገልገልን የሚመለከት ነው፤)

3. **ከማንኛውም የሰው ባለ ስልጣን/ኃያል ይልቅ እግዚአብሔርን የሚፈራ፡ -**
   ሐ ሥ 4፡18-20፣ ከጠሯቸውም በኋላ፣ በኢየሱስ ስም ፈጽሞ እንዳይናገሩና እንዳያስተምሩ አዘዟቸው። [19] ጴጥሮስና ዮሐንስ ግን መልሰው እንዲህ አሏቸው፤ "ከእግዚአብሔር ይልቅ ለእናንተ መታዘዝ በእግዚአብሔር ፊት ይገባ እንደሆነ እስቲ

እናንተው ፍረዱ፤ [20] እኛስ ያየነውንና የሰማነውን ከመናገር ወደ ኋላ አንልም።" በማለት መለሱላቸው። (5፡27-29፣ ዳን 3፡16-18)

4. **በጌታ ፍቅር አነሳሽነት የእግዚአብሔርን ቃልና መንፈስ ቅዱስን የሚታዘዝ/** የእግዚአብሔርን ቃል በመማር ተግባር ላይ በማዋል መልካም ፍሬ እያፈራ ዕድሜ ልኩን በመቀጠል ለሌሎች መልካም አርአያ የሚሆን ነው።

ዮሐ 8፡31 "ኢየሱስም ያመኑትን አይሁድ፦ እናንተ በቃሌ ብትኖሩ በእርግጥ (በእውነት) ደቀ መዛሙርቴ ናችሁ፤" (ዮሐ 9፡35-38፣)

ዮሐ 14፥21፣ "የሚወደኝ ትእዛዜን ተቀብሎ የሚጠብቅ ነው፤ የሚወደኝንም አባቴ ይወደዋል፤ እኔም እወደዋለሁ፤ ራሴንም እገልጥለታለሁ።" ዮሐ 14፡23

5. **ከራሱ ፈቃድ/ዓላማ/ዕቅድ/ፍላጎት ይልቅ የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያስቀድም።** ማቴ 16፡24 "ከዚያም ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን እንዲህ አላቸው፤ "ሊከተለኝ የሚወድ ራሱን ይካድ፣ መስቀሉንም ተሸክሞ ይከተለኝ፤"

ማንኛውም አማኝ የጌታ ደቀ መዝሙር የሚያሰኘው የእድገት ደረጃው ይለያይ እንጂ የራሱን የግል ፈቃድና ፍላጎት/ዕቅድና ዓላማ በመተው የጌታን ፈቃድ ማድረግን ያመለክታል።

ዕለት ዕለት ለራሱ ፈቃድ/ፍላጎት/ዓላማና ለኃጢአት በመሞት/በመተው በተለያየ ሰልፍ ቢያልፍም (ምንም ያህል ዋጋ/ሕይወትን ጭመር የሚያስከፍል ቢሆን ታግሶ፣ ዋጋ እየከፈለ የጌታን ፈቃድ በማድረግ) በጌታ በመታመን፤ ጌታን ደስ ለማሰኘትና እርሱን ለመምሰል በመስራት የሚጸና መሆን ነው። አንድ ሰው ሕይወቱን የሚመራው ጌታ ሳይሆን የራሱ ፍላጎት ከሆነ እውነተኛ የጌታ ደቀ መዝሙር አይደለም ማለት ነው። ይህ ማለት ግን ድነት በስራ ይገኛል ለማለት አይደለም። እውነተኛ/አክቲቭ እምነት በቃል ብቻ ሳይሆን በተግባርም ራሱን ስለሚገልጥ ከሙት/ዴድ/ እምነት በዚህ ተለይቶ ይታወቃል። (ገላ 2፡19-20)

6. **ከጌታ ጋር እንደሞተና ከእርሱም ጋር እንደተነሳ ለኃጢአት ሞቶ ለጽድቅ ሕይወት** እንደ ተነሳ በመቁጠር ለሃጢአት በመሞት/ኃጢአትን በመተው ጌታን በመከተሉ በተለያየ ፈተና ቢያልፍም እንኳ ጸንቶ በመቆም ባመነው ጌታ ታምኖ የሚቀጥል።

ሉቃ 14፡[27] ማንም መስቀሉን ተሸክሞ በኋላዬ የማይመጣ፤ ደቀ መዝሙሬ ሊሆን አይችልም።

ሉቃ 9፡23 "ከዚያም ለሁሉም እንዲህ አላቸው፤ "በኋላዬ ሊመጣ የሚፈልግ ማንም ቢኖር ራሱን ይካድ፤ መስቀሉንም በየዕለቱ ተሸክሞ ይከተለኝ፤" (ማቴ 7፡24-27፣ 1ጴጥ 1፡6-7)

**መስቀልን መሸከም ማለት፡-**

1. ኃጢአት ማድረግን ትቶ (ላኃጢአት ሞቶ/እንደ ሞተ ሰው ሆኖ) የእግዚአብሔርን ፈቃድ በማድረግ ለጽድቅ መኖርን (ለእግዚአብሔር በታዛዥነት መኖር) ማለት ነው።

2. ክርስቶስን ከመከተል የተነሳ በቤተሰብም ሆነ በሌሎች በጌታ ባመኑና ባላመኑ ወይም በተለያየ መልኩ በሚቃወሙት ሰዎች ዘንድ መናቅ፤ መገለል፣ ተቀባይነት/ተደማጭነት ማጣት፣ (rejection)
3. ልዩ ልዩ መከራ መቀበል፡-
   - የቅርብ ጓደኞችን ማጣት፣ ከቤተሰብ ጋር መለያየት፣
   - የሚተዳደሩበት ሥራ፣ ያገኙት የነበረ ጥቅማ ጥቅም፣ ሥልጣን ማጣት, መብት መነፈግ፡፡
   - የሚኖሩበት ቤትን፣ ያፈሩት ሃብትና ንብረትን ማጣት፤
   - የአካል ጉዳት አደጋ መድረስ፤
   - የሕይወት መስዋዕትነት መክፈል ድረስ የሚያደርስ መከራ መቀበልን ያመለክታል፣

በተለያየ ፈተና ቢያልፍም የሚጸና፣ ማር 4፡1-17፣ ማቴ 7፡24-27፣ ያዕ 1፡12፣1ጴጥ 1፡6-7፣

1 ጴጥ 1፡6-7፣ አሁን በብዙ ዐይነት ፈተና ውስጥ ሆናችሁ ለጥቂት ጊዜ መከራን ብትቀበሉም እንኳ በዚህ እጅግ ደስ ይላችኋል፡፡ [7] እነዚህ ነገሮች በእናንተ ላይ የደረሱት፣ በእሳት ተፈትኖ ቢጠራም፣ ጠፊ ከሆነው ወርቅ ይልቅ እጅግ የከበረው እምነታችሁ እውነተኛ መሆኑ እንደተረጋገጠና ኢየሱስ ክርስቶስ በሚገለጥበት ጊዜ ምስጋናን ክብርንና፣ ውዳሴን እንዲያስገኝላችሁ ነው፡፡

7. የሰዎች ሁሉ አገልጋይነት (ባሪያነት) ስሜትና አስተሳብ ያለው፡፡ በሰው ሁሉ ፊት እንደ ጌታ ሳይሆን እንደ አገልጋይ ራሱን ዝቅ በማድረግ ጌታ በሰጠው አገልግሎት የሚያገለግል፡፡ ዮሐ 13፡12-17፤
   1 ቆሮ 9፥19፣ "እኔ ነጻ ሰው ነኝ፤ የማንም ባሪያ አይደለሁም፤ ነገር ግን ብዙዎችን እመልስ ዘንድ ራሴን ለሰው ሁሉ ባሪያ አደርጋለሁ፡፡"

   መዝ 101፥6፣ "ከእኔ ጋር ይኖሩ ዘንድ፣ ዐይኖቼ በምድሪቱ ታማኞች ላይ ናቸው፤ በንጽሕና መንገድ የሚሄድ፣ እርሱ ያገለግለኛል፡፡" (በአካሄዳቸው ነቀፋ የሌለባቸው አገልጋዮቼ ይሆናሉ፤)

©ኤልያስ ታሪኩ (ደ/ር) 2018 ዓ.ም.